**Är du utsatt för våld i en nära relation? - Amhariska**

# በቅርብ ዝምድና መሓል ለአመጽ ኀይል ተዳርገዋልን?

በቅርብ ዝምድና መሓል ያለ የአመጽ ኀይል የተላያየ መልክ ሊኖረው ይችላል። ኣንዳንድ ጊዜ ነውጠኛው የኑሮ ጓደኛ ሊሆን ይችላል፥ አንዳንዴ ደግሞ የሥጋ ዘመድ። ወላጆቻቸውን ነውጥ ወይም ለአመጽ ኀይል የሚዳርጉ ልጆችም ኣሉ። ነውጡ በዓካል ወይም በኣዕምሮ ላይ ጉዳት ማድረስ፥ እንዲሁም በግብረ ሥጋ መድፈር ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል፥ አንድ ሰው

- በፀያፍ ቃል ከጠራዎት ወይም መጥፎ ስድብ ከሰደበዎት ወይም ደካማና መንቻካ እንደሆኑ እንዲሰማዎት ካደረገ
- ከገፈተሮት፥ ከመታዎት፥ ከቀላዎት ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ ጉዳት ካደረሰቦት፥
- ከተቆጣጠሮት ወይም ካገቶት፥ የማይፈልጉትን እንዲያደርጉ ካስገደዶዎት
- ኣመለካከትዎን ወይም የኣኗኗር ዘይቤዎን እንዲለውጡ ካስገደድዎት
- ግብረ ሥጋዊ ለሆነ ግንኙነት ካስገደድዎት
- በራስዎ ገንዘብ ላይ የገንዝብ ኣያያዝዎን የሚቆጣጠርዎ ከሆነ፥

ለነውጥ ተዳርገዋል ማለት ይቻላል።

**ጥበቃና ድጋፍ የማግኘት መብት ኣሎት**

ማንም ሰው በቅርብ ዘመዱ ለሚሰነዘርበት ነውጥ ሰለባ ሊሆን ይችላል። እርሶም ለዚህ ዓይነቱ ጥቃት የተጋለጡ ከሆነ መረጃ፥ ጥበቃና ድጋፍ ያገኛሉ፥ እንዲሁም ከበሬታና ልባዊ ኀዘኔታ የተሞላበት መስተንግዶ ይደረግሎታል። ይህ መብትዎ ነው። ልጅ ካልዎትም፥ ልጅዎ ጭምር ድጋፍ የማግኘት መብት ኣለው/ኣላት።

የሚከተሉትን ዓይነቶች ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ፥

- ውይይታዊ ድጋፍ
- ጥበቃና ጊዚያዊ መኖሪያ ቤት
- የኢኮኖሚ ድጋፍ
- ከባለሥልጣናትን ለምሳሌ ፖሊስ የማግኘት ድጋፍ፥

እንድንረዳዎት ያግኙን። ከፈለጉ ማንነትዎን ሳያሳውቁ ሊገናኙን ይችላሉ።

ለአስቸኳይ ጊዜ ሁሌም 112 ይደውሉ።

**ከእነዚህ ጋር ግንኙነት ያድርጉ፥**

- **ሥራው/ኀላፊነቱ:** Socialtjänsten Vårgårda
- **ስልክ ቁጥር:** Telefon växel 0322-600 617
- **ድረገጽ:** www.vargarda.se
- **ኣድራሻ:** Kungsgatan 45